አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፪/፲፱፻፺፱

# ስለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጣ አዋጅ

ደን የማልማት፣ የመጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ የመጠቀም ተግባር የሕብረተሰቡን የደን ውጤቶች ፍላጎት ለማሟላትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ባጠቃላይ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፤

የሀገሪቱን የደን ሀብት ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለውም ከመንግሥት ጎን ለጎን የህብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎና የጥቅም ተካፋይነት ሲረጋገጥ እንዲሁም የደን ፖሊሲና ኘሮግራም ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጋር ሲጣጣም በመሆኑ፤

በከፍተኛ ደረጃ ጎልቶ በሚታየው የሀገሪቱ ደን መመናመን ምክንያት እየተከሰተ ያለውን የአፈር መከላት፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት፣ የብዝሐ ሕይወት መመናመንና የግብርና ምርት ማሽቆልቆል ለመግታት የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ፤

በዚህም መሠረት የደን ልማትን ለማበረታታትና ውሱን የሆነውን የሀገሪቱን የደን ሀብት በአግባቡ ለመጠበቅና ለመጠቀም ስለደን ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በሥራ ላይ የሚውለው የፌዴራል መንግሥቱ በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሆኑን የሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ ፪(መ) ስለሚደነግግ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፪/፲፱፻፺፱ ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ «ሚኒስቴር» ወይም «ሚኒስትር» ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፫/ «ደን» ማለት በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው የለሙ በአብዛኛው ዛፎችና ሌሎች የእንጨትነት ፀባይ ያላቸው ተክሎች የሚገኙበት የእፅዋት ክምችት ነው፤

፬/ «ዛፍ» ማለት በዓይነቱ፣ በዕድሜውና በመጠኑ ሳይለይ የእንጨትነት ፀባይ ያለው ተክል ሲሆን ቀርከሀ፣ ሽመል፣ ዘንባባና ሚኒስቴሩ ዛፍ ብሎ የሚሰይመውን ተክል ይጨምራል፤

፭/ «የደን መሬት» ማለት ለደን ልማትና ጥበቃ ተብሎ የተከለለና በደን የተሸፈነ ሲሆን የቁጥቋጦ መሬትንና በከፍተኛ ተዳፋት ላይ የሚገኝ የተራቆተ መሬትን ይጨምራል፤

፮/ «የመንግሥት ደን» ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሆነ ማናቸውም ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደን ነው፤

፯/ «ጥብቅ ደን» ማለት ለተፋሰስ እንክብካቤና ለጄኔቲክ ሀብት፣ ለብዝሀ ህይወትና ባጠቃላይ ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ለሥልጠናና ለምርምር አገልግሎት እንዲውል ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲጠበቅና እንዲለማ የሚደረግ በዚህ አዋጅ መሠረት ጥብቅ ደን ተብሎ የተሰየመ ደን ነው፤

፰/ «ምርት ሰጪ ደን» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ምርት ሰጪ ደን ተብሎ የተሰየመ ለኢንዱስትሪና ለኮንስትራክሽን እንዲሁም ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የደን ምርት ሊመረትበት የሚችል ደን ነው፤

፱/ «የግል ደን» ማለት ከመንግሥት ደን ውጪ ሆኖ በማንኛውም ሰው የለማ ደን ሲሆን በገበሬ ማህበር አባላት ወይም በማህበር በተደራጁ ግለሰቦች፣ በባለሀብቶችና መንግሥታዊ በሆኑና ባልሆኑ ድርጅቶች የለማ ደንን ያጠቃልላል፤

፲/ «ሰው ሰራሽ ደን» ማለት በተፈጥሮ ከለማው ደን ውጭ በሰው አማካይነት ችግኝ በመትከል ወይም በሌላ ዘዴ የለማ ደን ነው፤

፲፩/ «የተፈጥሮ ደን» ማለት ማናቸውም በተፈጥሮ የበቀለ ዛፍ፣ ቁጥቋጦና ሌሎች የእንጨትነት ፀባይ ያላቸው ተክሎችና ዕፅዋቶች የበቀሉበት ደን ነው፤

፲፪/ «የቁጥቋጦ መሬት» ማለት በቁመታቸው እስከ 5 ሜትር የሆኑ እና የተበታተኑ የዛፍ ዝርያዎች የበቀሉበት የደን መሬት ነው፤

፲፫/ «የማኔጅመንት ኘላን» ማለት በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ደን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም የደን ሃብት በዝርዝር በማጥናት ለሃብቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም የሚወጣ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዕቅድ ነው፤

፲፬/ «የደን ውጤት» ማለት ዛፍ ወይም የዛፍ ተፈጥሮአዊ አካል የሆነ ወይም እንጨት ያልሆነ ማንኛውም ምርት ወይም በመጀመሪያ ደረጃ በሰው እጅ የተመረተ ወይም በፋብሪካ የተዘጋጀ የደን ምርት ነው፤

፲፭/ «የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ ፈቃድ» ማለት የደን ውጤቶችን ከማምረቻ ቦታ ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ ወይም ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ለማንቀሳቀስ የሚሰጥ፣ የምርቱን መነሻና መድረሻ የሚገልጽና ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤

፲፮/ «አግባብ ያለው የክልል አካል» ማለት ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በክልል መስተዳድር ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል አስፈጻሚ  አካል ነው፤

፲፯/ «የአካባቢ ህብረተሰብ» ማለት በመንግሥት እና በግል ደን አዋሳኝና በውስጡ የሚገኝ ውን ሕብረተሰብ የሚያጠቃልል ነው፤

፲፰/ «ኮንሴሽን» ማለት አንድን የመንግሥት ደን ሀብት በጥቅም ላይ ለማዋል ሲባል ለማንኛውም ሰው ለተወሰነ ጊዜ በውል ማኮናተር ነው፤

፲፱/ «ብዝሀ ህይወት» ማለት በደን ውስጥ ወይም በደን መሬት ላይ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የጥቃቅን ሕዋሣት ዘረመሎችና ዝርያዎች ክምችትና ስብጥር በተደጋጋፊነትና በአንድነት የሚገኙበትን ሥርዓተ ምህዳር የሚያጠቃልል ነው፤

፳/ «ሰው» ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ፫. <u>የደን ባለቤትነት ዓይነቶች</u>

የሚከተሉት የደን ባለቤትነት ዓይነቶች ይኖራሉ፤

፩/ የግል ደን፤ እና

፪/ የመንግሥት ደን።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የግል ደን ልማት፣ አጠቃቀምን ስለማስፋፋት</u>

## ፬. <u>የደን ልማትን ስለማስፋፋት</u>

፩/ ግለሰቦች፣ ማኅበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የንግድ ተቋማት ደን ለማልማት ሲፈልጉ በክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎች መሠረት ለደን ልማት ተብለው በተከለሉ ሥፍራዎች የገጠር መሬት የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።

፪/ በመንግሥት ይዞታ ሥር ባሉ ምርት ሰጪ ደኖች ውስጥ በኮንሴሽን ሊለሙ የሚችሉ የደን ቦታዎችን በመለየት ለሰው ሰራሽ ደን ልማት ተለይተው እንዲዘጋጁና እንዲሰጡ ሊደረግ ይችላል፡፡

፫/ በመንግሥት ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደንነት ያልተከለሉ ደኖችን ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመሆን የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ግለሰቦች፣ ማህበራት ወይም ባለሀብቶች በሚመለከተው አካል በሚወጣ መመሪያ መሠረት ጠብቀውና አልምተው እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡

፬/ የጥምር እርሻ ደን ዘዴ በይበልጥ በአርሶ አደሩ/በከፊል አርብቶ አደሩ ዘንድ እንዲሰርፅ ለማድረግ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የዕፅዋት ዘርና ችግኝ በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

፭/ ማንኛውም ደን አልሚ አካል በይዞታው በሚገኝ ወይም በኮንሴሽን ተከልሎ በሚሰጠው የመንግሥት ደን ውስጥ ለሚያለማው ደን የሚኖረው የባለቤትነት ዋስትና የተረጋገጠ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

፮/ የደን ባለይዞታዎች በደን መሬት የመጠቀምና ይዞታን የማስተላለፍ መብቶች በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ፫. የደን ቴክኖሎጂን ስለማስፋፋት

፩/ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያሉትን ሀገር በቀልና የውጭ እውቀቶች፣ ልምዶችና ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚው እውቀትና ክህሎት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

፪/ ለአርሶ አደሩ/ከፊል አርብቶ አደሩና ለግል ባለሀብቱ የሚቀርቡ የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆች ገቢን በማሳደግና በአጭር ጊዜ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ላይ ያተኩሩ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

፫/ በተለያዩ የግብርና ሥነ ምህዳር ቀጣናዎች ተስማሚ የሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ የደን ዝርያዎች የዘር አቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፬/ አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች በይዞታቸው ስር ያለውን የእርሻና የግጦሽ መሬት ከአፈር መሸርሸር ለመጠበቅና ለይዞታቸው ዳር ድንበር አገልግሎት የሚሆኑ የዛፍና የመኖ ዕፅዋት ዝርያዎችን በመምረጥ እንዲተክሉ፣ ያሉትንም እንዲንከባከቡ የሙያ እገዛ ይደረጋል፡፡

፭/ ደን በአግባቡ እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ጥቅም ላይ እንዲውል በደን ልማት ለተሰማሩ ሁሉ ዘመናዊ የደን ልማት ማኔጅመንት እውቀት እንዲኖራቸው ሥልጠናና ትምህርት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

፮/ የደን ውጤቶችን ለተለያዩ አገልግሎት እንዲውሉ ለማስቻል በመስኩ የተሰማሩ ሁሉ የሙያ ሥልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## ፮. <u>የደን ውጤቶች ገበያ ስለማስፋፋት</u>

፩/ አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ባለሀብቶች፣ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የንግድ ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁና ለገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የደን ውጤቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

፪/ የዛፍ ችግኝ በማፍላት ለተጠቀሚው ሕብረተሰብ ለሚያቀርቡ አካላት የሙያ እገዛ ይደረጋል፡፡

፫/ በደን ማኔጅመንት ፕላን መሠረት የደን ውጤቶች ለንግድና ለኢንዱስትሪ ልማት እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

፬/ ለደን ውጤቶች ንግድ የሚሰጠው ፈቃድ የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም በአገናዘበና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ በሚዘጋጅ የማኔጅመንት ዕቅድ መሰረት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

፭/ በገበያ ተፈላጊ ለሆኑ የዛፍ ዝርያዎች ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፮/ በደን ልማት ተግባር ለሚሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በደን ውጤቶች ግብይት ላይ ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

፯/ ባለሀብቶች በደን ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ማበረታቻዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡

፰/ ለአርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ለደን ባለሀብቶችና ድርጅቶች ያለሙትን ደን ውጤቶች ለገበያ በማቅረብ ረገድ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፡፡

፱/ የደን ውጤቶች ገበያ መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቅሮ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለደን አልሚና ተጠቃሚ ህብረተሰብ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## ፯. <u>የግል ደን አልሚዎች ግዴታ</u>

፩/ የግል ደን ተቆርጦ ከቦታ ቦታ ከመጓጓዙ በፊት ባለቤቱ የደን ሀብቱ ለሚገኝበት አካባቢ ላለው አካል በቅድሚያ በማሳወቅ የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፪/ የግል ደን ባለቤቶች፣

ሀ) በአግባቡ ደን የማልማትና የቆረጧቸውን ዛፎች በተለያዩ መንገዶች የመተካት፣

ለ) ደናቸው ከተባይና ከበሽታ ነፃ እንዲሆን ተገቢውን መከላከያ የማድረግ፣

ሐ) ባለሙት ደን ውስጥ ተባይና በሽታ ሲከሰት አግባብ ላለው አካል ሪፖርት የማድረግ፣

መ) ያለሙትን ደን ከቃጠሎና ከሌሎች ጉዳቶች እንዲጠበቅ የማድረግ፣ እና

ሠ) በአጠቃላይ የአካባቢ ደህንነትን፣ የተፋሰስና የብዝሀ ሕይወት ጥበቃንና በዓይነታቸው ልዩ የሆኑና በአካባቢው የሚገኙትን የተፈጥሮ ዛፎችንና የዱር እንስሳትን ጥበቃ በተመለከተ የሚወጡ መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው::

## ክፍል ሦስት

## ስለመንግሥት ደን ልማት፣ ጥበቃና አስተዳደር

### ፰. የመንግሥት ደንን ስለመሰየም፣ ስለመከለልና ስለመመዝገብ

፩/ የሀገሪቱን የደን ሀብት በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም ዋና ዋና የሆኑ የደን መሬቶች በመንግሥት ደንነትና በምርት ሰጪ ደንነት ተለይተው እንዲመዘገቡ ይደረጋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የክለላና የስየማ ተግባራት የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ የሚከናወኑ መሆን ይኖርባቸዋል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰየመና የተከለለ የመንግሥት ደን በሚገኝበት ክልል በሚወጣ ሕግ ዕውቅና እንዲያገኝ መደረግ ይኖርበታል::

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማንኛውም ደን ሲሰየምና ሲከለል የአካባቢውን ህብረተሰብ የማፈናቀል ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ባለው የመሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት በቅድሚያ የሕብረተሰቡ ጥቅም እንዲጠበቅ መደረግ ይኖርበታል::

### ፱. ስለመንግሥት ደን ልማት፣ ጥበቃና አስተዳደር

፩/ የመንግሥት ደን በአግባቡ እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና በጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል::

፪/ የመንግሥት ደኖች ካሉበት የልማት ደረጃ ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ የራሳቸው አስተዳደርና አመራር እንዲኖራቸው በተገቢው በጀት፣ የሰው ኃይልና ማቴሪያል እንዲሟሉ ይደረጋል::

፫/ የአካባቢው ህብረተሰብ በመንግሥት ደኖች ልማትና ጥበቃ ላይ እንዲሳተፍ፣ የልማቱም ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መርሃ ግብር ይቀየሳል::

፬/ የመንግሥት ደን ከተባይና ከበሽታ ነፃ እንዲሆን ተገቢውን መከላከልና ሲከሰትም በቁጥጥር ስር እንዲውል ይደረጋል::

፭/ የደን ሀብቱ ከተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ጥፋት እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

፮/ በመንግሥት ደን ውስጥ ለደኑ ልማትና ጥበቃ የሚያገለግሉ መመላለሻ መንገዶችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ይሰራሉ፡፡

፯/ ሰደድ እሳት እንዳይለቀቅ፣ ያለፈቃድ በደኑ ውስጥ ገብቶ መስፈር እንዳይኖር፣ የደን ምንጣሮ እንዳይካሄድ፣ ያለፈቃድ የማዕድናት ቁፋሮ እንዳይካሄድና ከመሳሰሉት ድርጊቶችና ከሌሎች አደጋዎች ደኑ እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

፰/ በደን ውስጥ የሠፈሩ ሰዎች ለልማቱ እንቅፋት በማይሆኑበት መንገድ ኑሮአቸውን የሚመሩበትና በልማቱና በጥበቃው ተግባር እንዲሳተፉ በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ወይንም በጥናት ላይ በመመስረት ከደኑ ውስጥ ወጥተው ሕይወታቸውን ሊመሩ በሚችሉባቸው ሥፍራዎች እንዲሰፍሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመወያየት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡

፱/ ደኑ ያለማቋረጥ ተፈላጊውን ጥቅም እንዲሰጥ በደን ማኔጅመንት ሥርዓት እንዲተዳደርና በዚሁ አኳያ ተገቢውን የቴክኒክና ተመሳሳይ ድጋፎች በማቅረብ ሥርዐተ ምህዳር እንዳይናጋ፣ የዱር እንስሳት መጠለያ እንዳያጡና ብዝሀ ህይወት እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

፲/ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ዘላቂነት ባለውና በተቀላጠፈ መንገድ መምራት ይቻል ዘንድ በፌዴራልና በክልል የተጠናከረ አካልና አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## ፲. <u>ስለመንግሥት ደን አጠቃቀም</u>

፩/ የመንግሥት ደን በጥቅም ላይ የሚውለው በሚዘጋጅና በሚፀድቅ የማኔጅመንት ኘላን መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ የመንግሥት ደን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጥቅም ላይ የሚውለው በመንግሥታዊ ድርጅቶች ወይም ደኑ በኮንሴሽን በተሰጣቸው ሰዎች ይሆናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አግባብ ያለው የክልል አካል የሚያዘጋጀውን የማኔጅመንት ኘላን በማይፃረር ሁኔታ የአካባቢው ህብረተሰብ ከመግንሥት ደን ውስጥ ሳር አጭዶ በመውሰድ፣ ደርቀው የወደቁ እንጨቶችንና ለመድሃኒትነት የሚውሉ ዕፀዋቶችን ወስዶ ሊጠቀም ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭(፫) ቢኖርም፣ በመንግሥት ደን ውስጥ የደን ውጤቶች እንዲሁም ሣርና ፍራፍሬ እንዲመረት ወይም የንብ ቀፎ እንዲሰቀል ለማድረግ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሊፈቀድ ይቻላል፡፡

፭/ የመንግሥት ደኖች ለቱሪዝም አገልግሎት እየዋሉ የገቢ ምንጭ እንዲያስገኙ ይደረጋል፡፡

## ፲፭. ስለጥብቅ ደኖች አስተዳደር

፩/ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖችና የደን መሬቶች ለአካባቢ ጥበቃ ካላቸው ጠቀሜታ፣ ለታሪክ፣ ለባህልና ለብዝሃ ሕይወት ጥበቃ እንዲሁም ለመስክ ትምህርት ከሚሰጡት ግልጋሎት አንጻር ዳር ድንበራቸው ተከልሎ እንዲጠበቁ ይደረጋል፡፡

፪/ ማናቸውም ደን፣

ሀ) የውሃ አካሎችን፣ የወንዞችን መነሻዎችና ተፋሰስን ለመጠበቅና ለማሻሻል፣

ለ) በብዛት የማይገኙና ለጥፋት የተጋለጡ የእፅዋት፣ የዱር እንስሳትና የአዕዋፍ ዝርያዎችን እንዲሁም በአጠቃላይ የጄኔቲክ ሀብቶችን ለመጠበቅ፣ ወይም

ሐ) ጎርፍን ለመቆጣጠር፣ አፈርን ከድርቀት፣ ከመሸርሸር፣ ከመከላትና ከመጠረግ ለመከላከል፣

ጥብቅ ደን ተብሎ ሊሰየም ይችላል፡፡

፫/ የጥብቅ ደንን ስፋት፣ አቀማመጥና የደን ዕፅዋት ስብጥርን ለይቶ መረጃ በማሰባሰብና በማጠናከር የአካባቢውን ሕብረተሰብ ያሳተፈና የብዝሀ ሕይወት ጥበቃን ግምት ውስጥ ያስገባ የደን ማኔጅመንት ፕላን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

፬/ በጥብቅ ደንነት የተሰየሙና እፅዋት የማይገኝባቸው ወይም በበቂ ደረጃ በእፅዋት ያልተሸፈኑ የደን መሬቶች በሚወጣላቸው የልማት ዕቅድ መሠረት እንክብካቤና ጥበቃ እንዲደረግላቸውና አስፈላጊ ሲሆን ደን እንዲለማባቸው ይደረጋል፡፡

፭/ በጥብቅ ደኖች ዙሪያ የደኑን ዳር ድንበር የሚያመላክቱና ለአካባቢው ሕብረተሰብ ለማገዶና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ፈጣን ዕድገት ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

፮/ ለአካባቢው ህብረተሰብ የደን ልማትና አጠባበቅ ትምህርት በመስጠትና በጥብቅ ደን ውስጥ በንብ ማነብ፣ ቅመማ ቅመም፣ የጫካ ቡና፣ የእንስሳት መኖና የመሳሰሉትን በማምረት እንዲጠቀሙ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፮. የደን ቃጠሎን ስለመከላከል

፩/ በደን ውስጥ ወይም በአካባቢው የሚኖሩ፣ የሚሠሩ ወይም የሚተላለፉ ሰዎች እሳት ከማንደዳቸው በፊት ተቀጣጣይ የሆኑ ነገሮችን ከአካባቢው በማስወገድ እሳት እንዳይነሳ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ የደን ቃጠሎ መነሳቱን የተረዳ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የመንግስት አካልና ማህብረሰብ ወይም ለሚኒስቴሩ የማሣወቅ ግዴታ አለበት::

፫/ የደን ቃጠሎ ሲነሳ በቅርብ የሚገኝ ጉዳዩ የሚመለከተው የክልል አካል ወይም ተወካዩ በአካባቢው የሚገኙትን መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትን እንዲሁም የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተባበርና በማንቀሳቀስ እሳቱን ለማጥፋት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት::

፬/ በአካባቢው የሚገኙ እንዲሁም ጉዳዩ በተለይ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋሞች እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ አባላት የተነሳውን የደን ቃጠሎ ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ የመሣተፍ ግዴታ አለባቸው::

## ፲፫. <u>የደን ውጤቶችን ስለማምረትና ስለማጓጓዝ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ተገቢ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው ከመንግሥት ደኖች የደን ውጤቶችን ማምረት አይችልም::

፪/ የደን ውጤቶችን ከቦታ ቦታ የሚያጓጉዝ ሰው በደን ውጤቶች ተቆጣጣሪዎች በሚጠየቅበት ጊዜ የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ ፈቃዱን የማሳየት ግዴታ አለበት::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን በመተላለፍ የተያዘ የደን ውጤት ሊበላሽ የሚችል ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የደን ውጤቱን በወቅቱ የገበያ ዋጋ ሸጦ ገንዘቡን በጉዳዩ ላይ የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ያስቀምጣል::

፬/ በመዘጋጀት፣ በክምችት ወይም በመጓጓዝ ላይ የሚገኙ የደን ውጤቶች በአዋጁ መሠረት የተፈቀዱ ስለመሆናቸው ማስረጃ እስካልቀረበባቸው ድረስ የአዋጁን ክልከላ በመተላለፍ የተገኙ እንደሆኑ ይቆጠራሉ::

## ፲፬. <u>ስለተከለከሉ ድርጊቶች</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በመጥፋት ላይ የሚገኙ ሀገር በቀል የተፈጥሮ ዛፎችን ከመንግሥት ደን ውስጥ ለመቁረጥ ወይም ለመጠቀም ሊፈቀድለት አይችልም::

፪/ ለመጥፋት የተጋለጡት የተፈጥሮ ሀገር በቀል ዛፎች ዝርዝር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፫/ ማንኛውም ሰው፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል የጽሁፍ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በመንግሥት ደኖች ውስጥ፣

ሀ) ዛፍ መቁረጥ፣

ለ) በጊዚያዊነት ወይም በቋሚነት መስፈር፣

ሐ) የቤት እንስሳትን ለግጦሽ ማሠማራት፣

መ) አደን ማካሄድ፣

ሠ) የእንጨት መሰጠንቂያ መጋዞችና ሌሎች ለደን ጭፍጨፋ የሚረዱ መሣሪያዎች ይዞ መገኘት፣

ረ) ቀፎ መስቀል ወይም ማር መቁረጥ፣አይችልም::

፬/ ማንኛውም ሰው በመንግሥት ደኖች ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶችን መውሰድ ወይም በእነዚህ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ማናቸውንም ተግባር ማከናወን አይችልም::

፭/ በመንግሥት ደኖች ውስጥ ሰፋፊ እርሻ፣ የማዕድን ሥራ፣ የመንገድ ሥራ፣ የውሃ ቁፋሮ፣ የመስኖና የግድብ ሥራ የመሣሰሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ለማካሄድ ወይም እነዚህኑ በተመለከተ የሥራ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር በቅድሚያ በመመካከር ስምምነታቸውን ማግኘት ያስፈልጋል::

## ፲፭. <u>ስለደን ጠባቂዎችና የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች</u>

፩/ የመንግሥት ደን ጠባቂዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ደኖችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ የተደነገጉትን በመተላለፍ ከሚፈጸሙ ድርጊቶች የመጠበቅ ሥልጣን ይኖራቸዋል::

፪/ የደን ውጤት ተቆጣጣሪዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት፣

ሀ) የደን ውጤቶችን የጫነ ወይም ለመጫኑ የሚጠረጠርን ማናቸውንም ማጓጓዣ በደን መግቢያና መውጫዎች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሚመረጡ የሀገር ውስጥ እና የድንበር መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ላይ አስቁሞ የመፈተሽ፣

ለ) የደን ውጤቶችን ሲያጓጉዝ፣ ሲያዘጋጅ ወይም አከማችቶ የተገኘ ሰው የደን ውጤቶቹን መነሻና መድረሻ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ወይም ማናቸውንም ሌላ ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ፣

ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተዘጋጅተው ሲጓዙ ወይም ተከማችተው የተገኙ የደን ውጤቶችን ከድርጊቱ ተጠያቂዎች ጋር የመያዝ፣

መ) ስለተያዙ የደን ውጤቶች ዝርዝር ሁኔታ ወዲያውኑ ለደኑ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፣ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሪፖርት የማድረግ፣ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል ::

፫/ የደን ጠባቂዎችና የደን ውጤት ዝውውር ተቆጣጣሪዎች በሥራቸው ላይ በሚሆኑበት ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወስነው መሠረት ዩኒፎርም የመልበስና መታወቂያ ወረቀት የመያዝ፣ በተጠየቁም ጊዜ የማሳየት ግዴታ አለባቸው::

## ፲፮. <u>የመጠቀም ግዴታና ስለማበረታቻ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሕገወጥ የደን ውጤቶች ዝውውርን፣ ዝግጅትን ወይም ክምችትን ለሚመለከተው አካል የመጠቆም ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሕገ ወጥ የደን ውጤቶች ጠቋሚዎችና ያዦች ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፯. <u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ሚኒስቴሩ፣

ሀ) አግባብ ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አካላትን በማስተባበር አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት አዋጁና በአዋጁ መሠረት የሚወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎችን በመከታተልና በመገምገም የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አዳዲስ የፖሊሲ ሀሳቦች እንዲነደፉና አስፈላጊም ሲሆን በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም ሕግ በየጊዜው እንዲሻሻል ያደርጋል፤

ሐ) በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያሉትን ሀገር በቀልና የውጭ ዕውቀቶች፣ ልምዶችና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በማዘጋጀት የደን አልሚውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲያድግ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

መ) በሀገሪቱ ስለሚገኝ ወቅታዊ የደን ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር የማያቋርጥ የመረጃ ልውውጥ መረብ እንዲኖር ያደርጋል፤

ሠ) የሀገሪቱ የደን ልማት የሀገር ውስጥ ፍጆታን በመሸፈን የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የደን ውጤቶችን ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ እንዲቻል ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመከታተል ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤

፪/ እያንዳንዱ ክልል በክልሉ ውስጥ የሚገኝን ማንኛውንም የመንግሥት ደን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ቢሆንም፣

ሀ) ደኑ በሚገኝባቸው አጎራባች ክልሎች በጋራ በአግባቡ ሊጠበቅና ሊለማ ያልቻለበት ሁኔታ ሲፈጠር፣

ለ) ደኑ በሚገኝበት ክልል ጠያቂነት በሚኒስቴሩ እንዲተዳደር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ሐ) ከደኑ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ አንፃር በሚኒስቴሩ ሥር ሆኖ መተዳደር የሚኖርበት ሁኔታ ሲፈጠር፣

ሚኒስቴሩ ደኑን ተረክቦ እንዲያስተዳድረው ሊደረግ ይችላል፡፡

## ፲፰. <u>የክልሎች ሥልጣንና ተግባር</u>

እያንዳንዱ ክልል፣

፩/ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም የመንግሥት ደን በዚህ አዋጅ መሠረት የማስተዳደር ሥልጣን ይኖረዋል፤

፪/ የሚያስተዳድራቸው የመንግሥት ደኖች እንዲሁም የግል ደኖችና የደን መሬቶች ተለይተውና የወሰን ምልክቶች ተደርጎባቸው ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፫/ አርሶ አደሩን/ከፊል አርብቶ አደሩን ያሳተፈ የደን ልማት ፕሮግራም እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬/ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የንግድ ተቋማት በደን ልማት ተግባር እንዲሳተፉ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፭/ የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆች ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፮/ ለደን ልማት በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ደን አልሚ መሬቱን ለደን ልማት ዓላማ ማዋሉንና በሚያዘጋጀው የደን ማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት መተግባሩን በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤

፯/ የደን ውጤቶች ሮያሊቲ ክፍያ ተመን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ፲፱. <u>የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ ፈቃድ</u>

የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የደን ውጤቶች ዝርዝርና መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳. <u>ቅጣት</u>

የተፈጸመው ጥፋት በወንጀል የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

፩/ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመንግሥት ደኖች ዛፎችን የቆረጠ ወይም የደን ውጤቶችን የወሰደ፣ ያዘጋጀ ወይም በማንኛውም መንገድ የተጠቀመ፣ ከ ፩ ዓመት በማያንስና ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ እስራት እና በብር ፲ሺ ይቀጣል፣

፪/ የደን የወሰን ምልክቶችን ያጠፋ፣ያበላሸ ወይም ያዛባ ከ ፩ ዓመት በማያንስ እና ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፣

፫/ እሳት በመለኮስ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በደን ላይ ጉዳት ያደረሰ፣ከ ፲ ዓመት በማያንስና ከ ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፣

፬/ በደን ክልል ውስጥ ያለፈቃድ የሰፈረ ወይም የእርሻ ቦታ ያስፋፋ ወይም ለማንኛውም የመሰረተ ልማት ግንባታ ያለፈቃድ በደን ቦታ የተጠቀመ ከ ፪ ዓመት በማያንስ እስራት እና በብር ፳ሺ ይቀጣል፣

፭/ ለሕገወጥ ደን ጨፍጫፊዎች ወይም የደን ውጤት አዘዋዋሪዎች በማንኛውም መልኩ ምርቱን እንዲደብቁ ወይም እንዲያሸሹ እገዛ ያደረገ በ ፭ ዓመት እስራት እና በብር ፭ሺ፣ መቀጫ ይቀጣል፣

፮/ ከላይ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፭ ባሉት ውስጥ ያልተጠቀሱና ቅጣት ያልተቀመጠባቸውን ጥፋቶች ያደረስ ከ፮ ወር በማያንስና አስከ ፭ ዓመት በሚያደርስ እስራትና እስከ ብር ፴ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፣

## ፳፩. <u>የተፋጠነ ሥነ ሥርዓት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ጥፋቶችን ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ የተያዘ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ አቅራቢያ ወደሆነው ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ የወንጀል ክስ እንዲመሰረትበትና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች እንዲፈጸሙ መደረግ ይኖርበታል፡፡

፪/ በሕገወጥ መንገድ የተገኘ የደን ውጤት ሲጓጓዝ በተገኘበት ተሽከርካሪ ወይም እንስሳ እንደተጫነ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ በእግዚቢትነት ከእነተሽከርካሪው ወይም እንስሳው መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ከተፈጸመ በኋላ ማጓጓዣው ወዲያውኑ መለቀቅ ያለበት ሲሆን፣ የደን ውጤቱ ግን የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ እንደተያዘ ይቆያል፡፡

፬/ የደን ውጤቶች ተቆጣጣሪዎች በሌሉበት አካባቢ የጉምሩክ ተቆጣጣሪዎች ወይም ፖሊስ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመያዝ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ የማድረግ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ የወንጀል ክሶችን በተፋጠነ ሁኔታ በማየት ውሣኔ ለመስጠት እንዲቻል ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ችሎቶችን ማደራጀት ወይም መደበኛ ችሎቶችን ማጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

## ፳፪. <u>የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች</u>

፩/ የደን ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፺፬/፲፱፻፹፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉደዩች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፫. ዝርዝር ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ደንቦችንና መመሪያዎችን እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤትና ሚኒስቴሩ ያወጣሉ፡፡

**፳፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት